# ለእግዚአብሔር ፍቅር

“… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48÷17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395

መጋቢት 1995 March 2003 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54÷13)
---------- አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ -------------

# ጸጋና ኃይል

“እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር።” “መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፦ እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።” (የሐ/ሥራ 6÷8) (7÷5-6)

እስቲፋኖስ ወንጌልን በመስበካቸው ከተሰውት ክርስቲያኖች የመጀመሪያው ነው። ኢየሱስ ያደረገለትን ለሕዝቡ በመናገሩ በድንጋይ ተወግሮ የተገደለ ደቀመዝሙር ነው። ይህ ሰው በታላቅ ቆራጥነት “ወንድሞችና አባቶች ሆይ ስሙ፤” እያለ መጽሐፍ ቅዱስን ሲገልጽላቸው ለነፍሱ እንደሚያሰጋው ጠፈቶት አልነበረም። ነገር ግን በብዙ ጽሎትና ምልጃ በመንፈስቅ ዱስም ሙላት ተዘጋጅቶ ስለነበረ ነው።

ጌታ “ኃይልንም ትቀበላላችሁ…” ሲል በሐዋሪያት ሥራ 1÷8 እንደ ተናገረው እስጢፋኖስ “መንፈስ ቅዱስን ተመልቶ” ስለነበረ÷የሚያጋጥመውን ማንኛውንም ሁኔታ ለመቀበል ኃይል ነበረው። ስለዚህም መስዋዕታዊ አርአያነቱ ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል አማኞችን ሲያበረታታ ኖሮአል።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት÷ ለአንድ ክርስቲያን ከምንም ነገር የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን በዚህ ማስተዋል ይቻላል። የክርስቶስን ቅድስና÷ሥልጣኑንና ክብሩን በሚታይ አኳኋን ማንጸባረቅ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተያልን? እግዚአብሔር ወደ ወደደው አቅጣጫ ቢመራህ ለመታዘዝ እስከማይቸግርህ ድረስ ÷ በመንፈስ ቅዱስ የተመላህ ነህ? እግዚአብሔር ለሕይወትህ ልዩና ታላቅ ዓላማ አለው። ራስህን ከኃጢአት በሚራቅ÷ ቃሉን በማጥናትና በጸሎት ከእርሱ ጋር ብዙ ጊዜ በማሳለፍ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ሕይወትህ ፍሬያማ ይሆናል። ይከናወንልህማል።

***************

# ጤና ይስጥልኝ

ቅባት የበዛበት ምግብ በጤና ላይ ስለሚያስከትለው ጠንቅ አስበው ያውቃሉ? ቅባት በዛ የሚባለው ምን ያህል ሲሆን ነው? ለምሳሌ የሚሆን የጥናት ውጤት እነሆ፦

በዚህ ጥናት ለምሳሌነት የቀረበው (wopper) ዎፐር የተባለው ሳንድዊች ነው። አስተናጋጁም በርገር ኪንግ (Burger King) የተባለው ምግብ ቤት ነው። እንደ ልማድ÷ ይህ ሳንድዊች የሚቀርበው÷ ከተጠበሰ ድንችና (fries) ከቀዝቃዛ መጠጥ ጋር ነው። ከወተት ከሚሠራ ጣፋጭ (milk shake) ጋርም ይታዘዛል።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው ፦ (milk shake) ወተትማው ጣፋጭ መጠጥ ÷ አንድ ዎፐርና አንድ የተጠበሰ ድንች፦ 2680 ሚሊ ግራም ሶዲየም እና 2710 ካሎሪዎች÷ 158 ግራም ቅባት ይገኝበታል።

በጤነኛ አመጋገብ አንድ ሰው በቀን መመገብ ያለበት የቅባት መጠን ከ30-40 ግራሞች ብቻ ነው። ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ቀላል መሳይ ምግብ÷ የአራት ቀን ቅባት በአንድ አፍታ እንደ መመገብ ነው፥ ሶዲየም ደግሞ ለደም ብዛት ዓይነተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ከጨው የሚገኝ ንጥረ ነገር ነው። አይገርምም?

*************

# ዕምነታችን፦

መጽሐፍ ቅዱስ፦ ስሕተት የሌለበት ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

እግዚአብሔር፦ ሥላሴ ሆኖ ለዘላለም የሚኖር ፈጣሪ÷ አንድ አምላክ ነው።
(ዘዳ 6÷4 እና ማቴ 28÷19)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ ከድንግል ማርያም የተወለደ÷ኃጢአት ያልተገኘበት÷ ተዓምራት ያደረገ ÷ ስለ በደላችን ተሰቅሎ የሞተ÷ ከሙታንም የተነሣ÷ ወደ ሰማይ ያረገና በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ÷ በታላቅ ክብር ዳግመኛ የሚመጣ አምላክ ነው። (ዮሐ/ወ 1)

የኃጢአት ስርየት፦ ማግኘት የሚቻለው በመናዘዝ÷ ንስሐ በመግባትና ለቤዛነት፥ በመስቀል ላይ የፈሰሰውን የክርስቶስ ደም በዕምነት በመቀበል ብቻ ነው።
(ዮሐ/ወ 14÷6)

ጥምቀት፦ በአብ÷ወልድ÷መንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ጥምቀት እናምናለን። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚለምኑት ያገኙታል። (ማቴ 28÷19፤ ሐዋ ሥራ 2÷4)

መንፈስ ቅዱስ፦ ክርስቶስን መስሎ ለመኖር፦ የቅዱሳን ረዳት÷ አጽናኝና መሪ የሆነው መንፈስ ቅዱስ የግድ ያስፈልጋል። (ገላትያስ 5÷16-25)

ትንሣዔ፦ ቅዱሳን÷ለዘለዓለም ሕይወት÷ ኃጢአተኞችም ለዘለዓለም ቅጣት÷ ከሙታን እንነሣለን። (ራዕይ 20÷11-25)

# ዓላማችን፦

ጸጋው በበዛልን መጠን÷ አማኞችን በቤተ ክርስቲያናቸውና በአካባቢአቸው ፍሬአማ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ማነቃቃት።

ወገኖቻችንን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር መጋበዝ።

# ጥበብ አሳሹ

በሩቅ ምሥራቅ አፈ ታሪክ አንድ ሰው ጥበብን ለማግኘት ምድርን ያስስ ነበር ይባላል። እርሱም ጠቢብ የሆነውን “ጉሩ” አግኝቶ ጥበቡን ለመካፈል ያልሞከረውና ያልደረሰበት ሥፍራ የለም፥



በእንዲህ እያለ፥ ከዕለታት አንድ ቀን ቸር ወሬ ሰማ። ጠቢቡ “ጉሩ” ሩቅ ሐገር በሂማላያ ተራራ ላይ በሚገኝ አንድ ዋሻ ውስጥ እንደሚኖር ተነገረው። በዚህን ጊዜ ጥበብ አሳሹ ፦ ጓዙን ጠቅልሎ÷ ፈረሱን ጭኖ ሸንተረሩንና በረሐውን አቋርጦ ወደ ሂማላያ ተራራ ገሰገሰ።

ለረዥም ጊዜ ከተጓዘ በኋላ፦ሂማላያ ተራራ ግርጌ ደረሰ። በዚያም እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጠባብ ሸለቆ መሐከል በብዙ ችግር አልፎ÷ ከጠቢቡ መኖሪያ ዋሻ ደረሰ። ከዚያም “በዓለም ሁሉ የታወቅኸው ጠቢብ አንተ ነህ ወይ?”“ጠቢብ ሆይ!” “ጠቢብ ሆይ” እያለ ይጣራ ጀመረ።

እጅግ ረዥም ጊዜ ተጠባበቀ። በመጨረሻም “ጉሩው” ሽማግሌ ከዋሻው ውስጥ ብቅ አለ። ጥበብ አሳሹም፦ “አባ ሽማግሌው÷ አስተዋይ መሆን የምችለው እንዴት ነው? ጥበብንስ ከየት አገኛለሁ?” ሲል ጠየቀው። ጠቢቡም ሽማግሌ÷በጉጉት የሚጠባበቀውን ጥበብ ፈላጊ ሰው÷ ዓይን ዓይኑን ትክ ብሎ እየተመለከተ÷ “ፈረስህን የምታገኘው የት ነው?” ሲል ጠየቀውና ሁለተኛ አንዳች ሳይናገር፦ ተመልሶ ወደ ዋሻው ገባ።

ፈረሱ ሁል ጊዜ ከእርሱ ጋር ነበረ!! ጥበብና የማስተዋል ችሎታ ሁል ጊዜ ከእርሱ ጋር ነበረ። በልቡ ውስጥ ነው። ጌታ ኢየሱስም በሉቃስ ወንጌል 17 ÷ 21 “እነሆ÷ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው።” እግዚአብሔር ለሕይወትህ እጅግ የሚጠቅሙ የጥበብ ነገሮችን ወደ ልብህ እየላከ ነው ፤ ነገር ግን እንደ ምናምን ቆጠርህ በቸልታ ታሳልፍ ይሆናል። ሃሳቡ አለህ። ራዕዩ አለህ። ችሎታውም አለህ። ነገር ግን ያለመብቃትህን ከሚገባህው በላይ ስለምታስብ በዕምነት ተነሥተህ አትሰማራም። ጥበብ እርሱም እግዚአብሔርን መፍራት÷ በልብህ አለ። ተነሣና ተሰማራ። የሰማይ አምላክ ያከናውንልሃል።

“ጥበብ በጎዳና ትጮኻለች በአደባባይ ድምፀዋን ከፍ ታደርጋለች፤በአደባባይ ትጣራለች፤ በከተማይቱ መግቢያ በር ቃልን ትናገራለች፦ እናንተ አላዋቂዎች÷ እስከ መቼ አላዋቂነት ትወድዳላችሁ? ፌዘኞችም ፌዝን ይፈቅዳሉ? ሰነፎችም እውቀትን ይጠላሉ? ”
(መጽሐፈ ምሳሌ 1 ÷ 20 – 22)

“የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ” (መጽሐፈ ምሳሌ 1 ÷ 6)

“በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን፦ እግዚአብሔርን ፍራ÷ ከክፋትም ራቅ፤ ይህም ለሥጋህ ፈውስ ይሆንልሃል ÷ ለአጥንትህም ጠገን።” (መጽሐፈ ምሳሌ 3 ÷ 7 – 8)

## ሁሉም ያልፋል

ከሰማይ በታች ለሚሆነው ሁሉ
ለንጋት ለምሽት ለአዳር ለመዋሉ
አንድም ነገር ሳይቀር ለፍጥረት በሙሉ
ለሁሉም ጊዜ አለው ተጽፏል በቃሉ፡፡

ሌሊት ሆኖ አይቀርም የመሸው ይነጋል
ፀሐይ ትጠልቃለች ንጋትም ይመሻል
እጅግ የጨቀየው የክረምቱ ወራት
የማያላውሰው የጭጋጉ ብዛት
ገለጥ ጠፈፍ ይላል ብራ የመጣ ዕለት፡፡

የአበቦች ወራት ደግሞ ፀደይ ሆኖ
የዕጽዋቱ ውበት ምድሪቱን ሸፍኖ
አምላክ ያደረባት ሐገር ገነት መስላ
ይህም ደግሞ ያልፋል ከወራት በኋላ፡፡

ሰይጣን የሰውን ጥረት አያመሳቀለ
ያሰቡት በሙሉ አልሳካ እያለ
ባንዱ ያዝሁት ሲሉ በሌላ ጫፍ ሲያመልጥ
መከራን ታግሰን ተግተን ስንጋፈጥ
ሁሉም ነገር ያልፋል ጊዜውን ጠብቆ
ፍሰሐ ይመጣል እንደ ንጋት አውቆ፡፡

ለሁሉ ጊዜ አለው ሎሚ ተራ ተራ
ልዩ ልዩ ሐዘን ያሁኑ መከራ
አምላክ የወሰነው ያበቃ ዕለት ቀኑ
እንደነጋበት ጅብ ሲሄድ ወደ ደኑ
ይህም ደግሞ ያልፋል ጊዜውን ጠብቆ
ፍስሐም ይመጣል እንደ ንጋት አውቆ፡፡

ከቀድመ አያት አያት በአባቶቻችንም
ከጥንቱ ነበረ በእኛ አልተጀመረም
ሐዘንና ደስታ ምሬትና እፎይታ
ይፈራረቃሉ እንደ ጧት ማታ
መውደቅን ያስብ ዘንድ የቆመ የሚመስለው
ለወደቀም ደግሞ ትንሣኤ እንዳለው
መከራ እንደሚያልፍ ጊዜውን ጠብቆ
ፍስሐም ይመጣል እንደ ንጋት አውቆ፡፡

መላኩ ትዕዛዙ

የዚህ አገልግሎት ጠቃሚነት የሚታያችሁ ሁሉ፡-ጸጋው እንዲበዛልን ፀልዩልን፡፡ ዓለም አቀፍ የፖስታ ዋጋን ለመሸፈን የሚቻለውን ያክል በዓመት ልትረዱን የምትፈቅዱ÷እንድትተባበሩን በእግዚአብሔር ፍቅር እንጠይቃችኋለን፡፡ በቅርብ ጌታ ቢፈቅድ የዌብ ገጽ ይኖረናል፡፡

# ምስክርነት

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ÷ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ፡" (የሐዋ ሥራ 1÷8)

የሚከተለው ግሬግ ላውሪ የተባለ ደራሲ ስለ ራሱ የምስክርነት ልምምድ (How to share your Faith) በሚለው መጽሐፉ ከጻፈው የተዘጋጀ ነው፡፡)

ስለ ጌታ ኢየሱስ ለሰው መናገር እጅግ ከሚጨንቃቸው ሰዎች ዋናው ነበርሁ፡፡ ይሁን እንጂ ጌታን በወጣትነቴ እንደ ተቀበልሁ÷ በቤተ ክርስቲያናችን ስለ ምስክርነት በኃይል ያስተምሩን ስለ ነበረ÷ ምርጫ አልነበረኝም፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የማይመሰክር ክርቲያን የሕሊና ዕረፍት አልነበረውም፡፡ ስለ ዚህ እኔም አንድ ቀን በምኖርበት ከተማ አጠገብ ወደ ነበረው ባሕር ዳር÷ የምመሰክርለት ሰው ፍለጋ ወጣሁ፡፡

ጌታን ከተቀበልሁ ገና ሁለት ሳምንቴ ስለ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስን ሆነ የክርስትናን ሕይወት ምንም አላውቅም ነበር፡፡ ዕምነታችሁን ለሰዎች መስክሩ ብለው ስላስተማሩኝ ብቻ ነው የወጣሁት፡፡ በራሴ ምንም መተማመን አልነበረኝም፡፡ የማይከራከርና የማይቆጣ ሰው እንዲያጋጥመኝ እየፀለይሁ ሰዎች በማይታጡበት ባሕር ዳር (beach) መመላለስ ጀመርሁ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓይኔ በአንዲት የእናቴ እኩያ የሚትመስል÷መካከለኛ ዕድሜ የደረሰች ወይዘሮ ላይ አረፈ፡፡ የማትጨክንብኝና የምትሰማኝ መስላ ታየችኝ፡፡ ወደ እርሷ በቀረብሁ ጊዜ ግን ከመፍራቴ የተነሣ ድምፄ ጎረነነና ተንቀጠቀጥሁ፡፡ ቃላት ለማማረጥ እየሞከርሁ፡- "እ-እ- ይቅርታ÷ ስለ አንድ ነገር ላነጋግሽ?" አልኳት፡፡ እርሷም "አዎን፤ ስለ ምን ድን ነው?" አለችኝ፡፡ እኔም "ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንግሥተ ሰማይ ነገር" አልኳት፡፡ (የአሥራ አምስት ዓመት ያህል ልጅ ነበርሁ) የሚደንቀው ነገር ግን ሴትየው፡ "ምን አለበት? ተናገር፡፡ እሰማሃለሁ፡፡" ስትል መለሰችልኝ፡፡

ከዚያም ቶሎ ብዬ ለእንዲህ ያለ ጊዜ ኪሴ ውስጥ ይዤ የነበረውን ትራክት ሳብ አደረግሁ፡፡ በዕምነቴ በጣም አዲስ ከመሆኔ የተነሣ አንዳች ነገር በቃሌ አላጠናሁም ነበር፡፡ ስለዚህ ትራክቱን ከጅማሬ አስከ ፍጻሜ አነበብሁላት፡፡ በማነብበትም ወቅት እንቀጠቀጥ ነበር፡፡ መቼም ምስክርነቴ ይሰራል ሴቲቱም ጌታን ትቀበላለች ብዬ አላሰብሁም፡፡ ነገር ግን ሴቲቱ የማነበውን ሁሉ በጥሞና ሰማች፡፡

እያነበብሁላት ወደ መጨረሻው ስደርስ፡- "አሁን ጌታን የማትቀበይበት ምክንያት ይኖርሻል?" የሚለው ላይ ደረስሁ፡፡ ወዲያውም ይህንን ጥያቄ ልጠይቃት? አልጠይቃት? እያልሁ ወላወልሁ፡፡ ከዚያም ልብ ገዛሁና÷"አ- አሁን ጌታን የማትቀበይበት ምን ምክንያት ይኖራል?" አልኳት፡፡ እርስዋም፡- "ምንም" አለችኝ፡፡ እኔም በድንጋጤ ልቤ እንደ ከበሮ እየመታ÷ማመንም ስላቃተኝ "እና አሁን ጌታን ትቀበያለሽ?" አልኳት፡፡እርስዋም ሳታቅማማ "አዎን" አለችኝ፡፡

እኔም ይህን ሁሉ ስኪት ስላልተጠባበቅሁ ፡- ለትንሽ ጊዜ ግራ ተጋባሁ፡፡ ከዚያም በመደናገር በትራክቱ ላይ የንስሐ ፀሎት የሚገኝበትን ቦታ ፈለግሁ፡፡ ብዙ ካስቸገረኝ በኋላ አገኘሁት፡፡ ከዚያም እጅግ እየፈራሁ በታላቅ ትሕትና፡- "በይ እንግዲህ ÷ አንገታችንን ዝቅ አድርገን እንፀልይ" አልኳት፡፡ እርስዋ ተከትላኝ አየፀለየች እንኳን እኔ ግን በልቤ "ይኸ የማይሆን ነገር ነው" እያልሁ አስብ ነበር፡፡

ፀሎታችንን እንደፈጸምን ሴትየው ቀና ብላ አየችኝና "አንድ ነገር ሆኜአለሁ፡፡ ልዩ ደስታ ይሰማኛል፡፡" አለችኝ፡፡ ወዲያው በእኔም ይኸ ነው የማይባል የመንፈስ ቅዱስ ደስታ ወረደብኝ፡፡ በዚያም ቀን እግዚአብሔር በሕይወቴ ሲሠራ የመጀመሪያዬን ቅምሻ አገኘሁ፡፡ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ወንጌልን ለሰዎች መንገር ግዴታዬ መሆኑን በእርግጠኝነት የተረዳሁት ያኔ ነበር፡፡

## ለምስክርነት ከሚያስፈልጉ ነገሮች ጥቂቶቹ፡-

**ሸክም፡-** ሸክም ጌታን የማያመልኩ ሰዎች ወደ ዘላለም ስቃይ መሄዳቸውን ከማስተዋል የሚመጣ ለሚጠፉት የማዘን ጸጋ ነው፡፡ ሲያል በዕውነት አሰቃቂና ማንም ሊሄድበት የማይገባ ክፉ ሥፍራ መሆኑን ከመረዳት የሚነሣ ለሰዎች የማዘን (የፍቅር) ኃይል ነው፡፡ ሸክም የራስን ቤተ ክርስቲያን አባላት የማብዛት ፍላጎት አይደለም፡፡ ሰው ሁሉ እንደ እኔ ይሁን የማለት ስሜትም አይደለም፡፡ የዕውነተኛ ሸክም ዋና ዓላማው ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ ነው እንጂ ሌላ ምድራዊ ዓላማ አይደለም፡፡ ይህንን ዓይነት ሸክም ካለን በዕውነት መመስከር ችግር አይሆንብንም፡፡

የነፍሳትን ፍቅርና ሸክምን ግልጽ ለማድረግ ተጨማሪ መግለጫ እንይ፡- በመንገድ ስንተላለፍ ታላቅ የጭንቀት ጩኸት እንሰማለን እንበል፡- ዞር ብለን ስንመለከት ወየው ወየው ልጄ÷እያለች የምታለቅስ እናት በሚጋይ ቤቷ ፊት ስትንጎራደድ እናያለን፡፡ ሕጻን ልጅዋ በሚነድደው ቤት ውስጥ እንደ ሆነና ሕጻኑን ለማዳን ያለን ዕድል እጅግ የተወሰነ መሆኑን እንረዳለን እንበል፡፡ በዚህ ሁኔታ ምን ይደረጋል? ሕጻኑ የእኔ አይደለምና በማለት÷ ጥለናት እናልፋለን? አይመስለኝም፡፡ አይዞሽ ምንም አይደለም÷ተጽናኚ ልንላት እንችላለን? አይደረግም፡፡ ለራስ በሚያሰጋ እሳት ውስጥ ዘልለን በመግባት ሕጻኑን ለማዳን እንሞክራለን? አዎን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የማይከተሉትን የሚጠባበቀው እሳት ከዚህ የከፋ ነው፡፡ ምክንያቱም ዘላለማዊ እሳት ነው፡፡ ከዚያም መመለስ የለም፡፡ የዘላለም ስቃይ ነው፡፡ ታድያ ይህ ሊገደን አይገባም? የፍቅር ሰውና ጥሩ ክርስቲያን ነኝ የምንል÷ እግዚአብሔርን እወዳለሁ የምንል÷ በዚህ ሊገደን አይገባም? በዕውነት ሸክም ሊኖረን አይገባም?

ለሰዎች ስለ ጌታ ስንነግር ከፍቅር ሸክም ከሆነ ይረዳሉ፡፡ ከኃይማኖታዊ ግዴታ ብቻ ከሆነም ይረዳሉ፡፡ ደረቅ ኃይማኖታዊ ጥያቄና መልስ ይዘው ለሰዎች ለመመስከር የሚወጡ ሰዎች አይቼ አውቃለሁ፡፡ ይህም ያለ ፍቅር÷ ከሸክም ያልሆነ የሽንፈት ምስክርነት ነው፡፡ ስለ ፍቅር ቀኑን ሙሉ ልናወራ እንችላለን፡፡ ብዙ የግሪክና የዕብራይስጥ ቃላት መግለጽ እንችላለን፡፡ ስለ መንግሥተ ሰማይም በርካታ ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ማውጣት እንኳን እንችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ዕምነታችን የሰዎችን ልብ መንካት የሚችለው÷ ለሚጠፉት ርኅራኄና ሸክም ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ ያም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ በፀሎት ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ሆነ ለሚለምኑ ይሰጣል፡፡ ...... ይቀጥላል

ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡